**ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ**

**<u>አዲስ አበባ</u>**

**ጉዳዩ፡- <u>የነፃ ትምህርት (scholarship) እድል መስጠትን ይመለከታል</u>**

ሳንድፎርድ ኢንተርናሽናል ት/ቤት እ.ኤ.አ. በ1949 የተመሰረተ ሲሆን በInternational Baccalaureate (IB) እና International General Certificate of Secondary Education (IGCSE) ካሪኩለሞች ለኢትዮጵያውያንና አለም አቀፍ ማህበረሰብ ልጆች ትምህርት እየሰጠ ይገኛል፡፡

ት/ቤታችን ከዚህ ከዋናው የማስተማር ተግባሩ በተጨማሪ ለማህበረሰቡ በተለያየ መንገድ ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍ(community service) በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ ት/ቤታችን ለማህበረሰቡ ከሚያደርጋቸው ድጋፍ መካከል በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ የመንግስት ት/ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች መካከል በትምህርታቸው የላቀ ውጤት ለሚያመጡ ተማሪዎች በየዓመቱ የነፃ የትምህርት ዕድል(scholarship opportunity) ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

አሁንም ት/ቤታችን ለ2018 የትምህርት ዘመን የመንግስት ት/ቤት ተማሪዎችን ከ7ተኛ ክፍል ጀምሮ የነፃ ትምህርት እድል ተሰጥቷቸው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ለማድረግ ዝግጅቱን አጠናቋል፡፡በዚሁ መሠረት የትምህርት ቢሮው ከስር የተጠቀሰውን የመመልመያ መስፈርት የሚያሟሉ ከሠላሳ እስከ አርባ ከስድስት ወደ ሰባተኛ ክፍል የሚዛወሩ የመንግስት ት/ቤት ተማሪዎችን በአዲስ አበባ ከተማ ከሁሉም ክፍለ ከተሞች ከሚገኙ ት/ቤቶች ተማሪዎችን ከነሙሉ አድራሻቸው እንዲልክልን እየጠየቅን ለሚደረግልን ትብብር በቅድሚያ እናመሰግናለን፡፡

በተጨማሪም መስፈርቱን የሚያሟሉ ተማሪዎች በአካል ት/ቤታችን ድረስ መተው ማመልከት የሚችሉ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

***<u>የመመልመያ መስፈርቶች</u>***

1. ተማሪዎቹ ኢትዮጲያዊያን የሆኑ እና በመንግስት ት/ቤቶች ውስጥ በ2017 ዓ.ም የ6ተኛ ክፍል ተማሪ የሆኑ
2. በ2017 ዓ.ም. በ6ተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና 96 እና ከዛ በላይ ፐርሰንታይል ያመጡ
3. ከሚማሩበት ትምህርት ቤት ስለ ጥሩ ፀባያቸው፣ የትምህርት ውጤታማነታቸው እንዲሁም በትምህርት ገበታ ላይ በሰአቱ የመገኘት ልምድ እንዳላቸው የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ
4. የእንግሊዘኛ እና የአስተውሎት ችሎታ (CAT4) ፈተና ለመውሰድ ፈቃደኛ የሆኑ
5. ዕድሜያቸው ከአስራ አንድ እስከ አስራ ሶስት ዓመት የሆነ
6. ራስን ለማሻሻል ቀና የሆነ አመላካከት ያላቸው
7. ከዚህ ቀደም ይማሩ ከነበረበት ትምህርት ቤት ጥሩ ውጤት ያመጡ እንደነበር የሚያሳይ ማስረጃ
8. ከት/ቤታቸው ሳንድፎርድ ኢንተርናሽናል ት/ቤት ለሚሰጠው ነፃ የትምህርት ዕድል የታጩ መሆናቸውን የሚያሳይ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችሉ
9. ሳንድፎርድ ኢንተርናሽናል ት/ቤት የሚሰጠውን ተጨማሪ መመዘኛ እና ክራይቴሪያዎች የሚያሟሉ

ከሠላምታ ጋር

ማማሩ ግስላው
የኢንተርናል ኦዲት እና ቁጥጥር ኃላፊ